ከሩቅ ዘመድ ፡ የቅርብ ጐረቤት ።

በሩቅ ቦታ ላይ ከሚኖር የሥጋ ዘመድ ይልቅ ፡ በቅርብ ቦታ ላይ የሚኖር ባዕድ የሆነ ጐረቤት ይሻላል ፤ ምክንያቱም የሩቅ ዘመድ ስለ ዘመዱ ማንኛውንም ነገር የሚሰማው በጣም ዘግይቶ ሲሆን ፤ የቅርብ ጐረቤት ግን ፡ የሥጋ ዝምድና ባይኖረውም እንኳ የአብሮ መኖር ግዴታ ስላለበት ፤ ቀንም ሆነ ሌሊት ፡ ጥዋትም ሆነ ማታ ፡ በሚያስፈልገው ጉዳይ ጐረቤቱን ለመርዳት ፈጥኖ የሚደርስ በመሆኑ ነው ።

ከአብሮ አደግህ ፡ አትሰደድ ።

የሰው ፡ ጠባይ በቅንዓትና በምቀኝነት ስለሚሸነፍ ፤ አብሮ አደግህ ራሱን ከፍ ከፍ እያደረገ ፡ የአንተን የባልንጀራውን ግብርና ዘር በመጥፎ ሁኔታ እያቄሸሸ ፤ በሰው አገር ላይ እንደሚአወራብህ ፤ የተረጋገጠ ነው ፤ ስለዚህ ከአብሮ አደግህ ጋር ወደ ሰው አገር ከቶ አብረህ አትሰደድ ።

እግዚአብሔርን ከማይፈራ ወዳጅ ፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጠላት ።

እግዚአብሔርን ከማይፈራ ግብዝ ወዳጅ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ ብርቱ ጠላት ይሻላል ፤ ምክ

ንያቱም እግዚአብሔርን የማይፈራ ወዳጅ «ባንተ ላይ ሊአደርገብህ የማትወደውን ነገር ፡ በሌላ ሰው ላይ አታድርግ ፤ » የሚለውን ትእዛዝ የማይፈጽም በመሆኑ እንዳይጠረጠርም ወዳጅነቱን ጋሻ አድርጎ በቀላሉ ሊአጠፋ ስለሚችል ነው ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጠላት ግን ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር እየተወ ፡ እውነተኛውን ፍርድ በትዕግሥት ይጠባበቃል እንጂ ፤ በገዛ እጁ መበቀሉ ቀርቶ ፡ የጠላቱን ስም እንኳ በክፉ ሳያነሣ ፤ ጠልቶ ዝም ስለሚል ብቻ ነው ።

ከማይራገጥ ፡ ወተቱን ፤ ከማይናገር ፡ ከብቱን ።

ከማይራገጥ የቤት እንስሳ ዘንድ ፡ ወተቱን ማለብ ምቹ እንደሆነ ፤ እንዲሁም ፡ ነገርን ከማያውቅና ከሚጠላ ሰው ዘንድ ፡ ከብቱን ፡ ወይም ሀብቱን መንጠቅ ፤ ይጠቅማል ፤ ምክንያቱም ፡ በፍርድ ቤት ከሶና ተሟግቶ ገንዘቡን ማስመለስ ፡ ጥፋተኛውንም ማስቀጣት ስለማይችል ነው ፤ ማለት ፤ አይገባም ።

ዳዊትና ሚስት ፡ በብዙ ።

በአስራኛው ሰዓት ላይ «አቤቱ! ልመናዬን ስማኝ ቃሌንም አድምጥ ! » እያሉ ለመድገም እንዲመች ፡ ዳዊትን ከብዙ ፤ አለ መለየት ነው ። እንዲ

ሁም ፡ የሔዋን ልጆች ባሕርይ እጅግ ደካማ በመሆኑ ምክንያት ፡ ለማረጋጋትም ሆነ ፡ ከመጥፎ ነገር ለመ ጠበቅ እንዲመች ፡ ሚስትን ከአጠገብ አለ ማራቅ ፡ መልካም ነው ።

ከባለቤቱ ያወቀ ፡ ቡዳ ነው ።

ከጥቅሙ ባለቤት ይልቅ ፡ ወይም ከባለጉዳዩ ይበልጥ ፡ ለሌላው ሰው ያወቀ « ቡድሃ » የተባለው ሰው ነው ፤ ምክንያቱም ቡድሃ ለብዙዎቹ የዓለም ሕዝቦች የተሰወረውን የፍልስፍና ምሥጢር ከዕድለ ኛው ሰውነቱ እያፈለቀ ፤ ዘለዓለማዊ ምክሩን ስለ አስተማረና ለመላው ዓለምም ስለ ተረፈ ነው ።

ከብት ፡ አይወድም ገደል ፤ ሰው ፡ አይወድም በደል ።

ከብት ለምለም ሣርን አይቶ እበላለሁ ሲል ፤ ድንገት የሚውጠውን ገደል ፡ ወይንም ጉድጓድ እንደ ማይወድና ፤ እርሱንም አይቶ እንደሚበረግግ ፤ እንዲ ሁም ፡ ሰው ፡ በዚህ ዓለም ላይ በሰላም እኖራለሁ ፤ ብሎ ሲመኝ ፤ ድንገት ከአንዳንድ ክፉዎችና ከሚያም ናቸውም ሰዎች ዘንድ ፡ የሚፈጸምበትን በደል አይወ ድም ።

ካልታረደ ፤ አይታይ ስባቱ ፤ ካልተናገረ ፤ አይታይ ብልሐቱ ።

ከብቱ ታርዶ ቆዳው ካልተገፈፈ በስተቀር ፤ የሥጋው ስባቱ ፡ ወይም ጮማነቱ ፡ አይታይም ። እን ደዚሁም ፡ ልዩ ልዩ ጥበባትን የተማረ ሰው ፡ « ይህ እንዲህ ይሆናል ፤ ያም ፡ እንደዚያ ይደረጋል ፤ » እያለ የማያውቁትን ሰዎች ለማስረዳት ካልተናገረ ፤ ብልሐቱ የጋን መብራት ይሆናል እንጂ ፤ በግልጽ አይታይም ።

ከሳሽ ፡ የተከሳሽን ልብ ቢያውቅ ፤ ከቤቱም ባልወጣ ።

ከሳሽ ላቀረበው ክስ ተከሳሽም በበኩሉ የሚሰ ጠውን መልስ አስቀድሞ ቢያውቅ ኖሮ ፤ ሥራውን ፈትቶ ፡ ገንዘቡን አውጥቶ ፡ ባላጋራውን ለመክሰስ ፡ ወደ ፍርድ ቤት ባልሔደ ፤ ወይም ደግሞ ሌላ ክስ ባዘጋጀ ነበር ።

እንጀራ እንጀራው ከባዕድ ፤ መከራ መከራው ከዘመድ ።

እየተደሰቱ እንጀራውንና ጮማውን ፡ ማሩንና ቅቤውን ፡ አትክልቱንና ፍራፍሬውን ፡ ከባዕድ ጋራ መኰምኰም ፤ እየጨፈሩም ፡ ወተቱን ፡ ጠጁንና ጠላ ውን ፡ ከባዕድ ጋራ መላፍ ፡ የኃዘኑን ፡ የመከራውንና

የድኽነቱን ጊዜ ብቻ ግን ፡ ኩርምት ብሎ ከቤተ ሰብና ከዘመድ ጋራ ማሳለፍ ፡ እርቀውና ጠልቀው እየተመ ራመሩ በማያስቡ ሰዎች ዘንድ የተለመደ ነው ፤ ይሁን እንጂ አድራጎቱ እጅግ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስ ተዛዝብ ነው ።

እገድል ያለ መጋኛ ፤ እበላ ያለ ዳኛ ።

ሰውንና እንስሳን ላይምር የመጣ መጋኛና ፡ ጉቦን እበላለሁ ያለ ዳኛ ፡ አንድ ናቸው ፤ ምክንያቱም ሰውን ፡ ወይም እንስሳን በእርግጥ ሊገድል የመጣ መጋኛ ፡ ምንም እንኳ ባለማቋረጥ ቢታከሙትም ቅሉ ፤ ያደረበትን እያሰለሰለውና እያደከመው ቂይቶ በመጨ ረሻ ከዚህ ዓለም ላይ በሞት ጭልፊት ጠልፎ ስለሚ ወስደው ነው ። እንዲሁም ከየባለ ጉዳዩ ዘንድ ጉቦ መቀበልን የለመደና አሁንም ጉቦን መብላት አለብኝ ብሎ ፡ ቁርጥ ሐሳብ ያደረገ ጉቦኛ ዳኛ ፡ ነገሩ እንዳይ ፈጸም ምክንያትን በመፍጠር ፤ ቀጠሮን በቀጠሮ እያ ስተላለፈ ባለጉዳዩን አጉላልቶ ፡ ገንዘቡንም በልቶ በኾለት ፊት ስለሚጐዳው ነው ።

እሾህ አጣሪውን ፤ ነገር ሠሪውን ።

በቦታው ላይ ሌላ ሰው ፡ እንዳይተላለፍበት ተብሎ የሚታጠረው እሾህ ፡ አጣሪውን ሰውዬ እንደ

ሚወጋው ሁሉ ፤ እንዲሁም በጉዳዩ ሌላ ሰው እንዳይ ጠቀም ተብሎ የሚሠራው ክፉ ነገር ፡ ሠሪውን ብቻ ተመልሶ እልም አድርጎ ያጠፋዋል ማለት ነው ።

የመነኰሴ ሎሌ ፤ የክረምት አሞሌ ።

የመነኰሴ ሎሌና የክረምት አሞሌ አንድ ናቸው ፤ ምክንያቱም የመነኰሴ ሎሌ ከሚሠራበት ጊዜ ይልቅ «ዛሬ ማርያም ነች ፤ ነገም ጊዮርጊስ ነው ፤ ዳዊት እደግማለሁ ፤ ቤተ ክርስቲያን እስማለሁ ፤ » እያለ ሥራ የሚፈታበት ጊዜ ይበልጣል ። በጦርነት ጊዜም «አትግደል» የሚለውንና ራሱም በጭካኔ ተገድሎ እን ዳይሞት ከመፍራቱ የተነሣ ፤ ጌታውን ትቶ ይሸሻል እንጂ ፤ የሚፈለግበትን ተግባር አያበረክትም ። እን ደዚሁም የክረምት አሞሌ እርጥበት በተሰማው ቍጥር ፤ አብሶ ዝናብ የነካው እንደ ሆነ ፤ እንደ በረዶ ሙምት ብሎ በመፍረስና እንደ ቅቤም በመቅለጥ ጨው ነጋ ዴውን በከፍተኛ ኪሣራ ላይ ስለሚጥለው ነው ።

ልጅ ፡ እየመከሩት ያጠፋል ፤ እጅ ፡ እየታጠቡት ያድፋል ።

ልጅ በእጅ ይመሰላል ፤ ምክንያቱም ፡ እጅ በየ ደቂቃውና በየ ቅፅበቱ ላይ የማያርፍ መሣሪያ ከመ

ሆኑ የተነሣ ፤ ብዙ ጊዜ እየታጠቡት መልሶ መልሶ ስለሚያድፍ ፤ ሲሆን ፤ ልጅ ደግሞ ማንኛውንም ነገር ፈጥኖ የሚረሳና በጨዋታም የሚታለል በመሆኑ ፡ በየጊዜው እየመከሩት ፡ እየተቁጡትና እየቀጡት ፡ ወዲያው ሲአጠፉ ስለሚገኝ ነው ።

የዘመኑ ሰው ፡ መላሱ መንታ ፤ አንዱ ለምስጋና አንዱ ለሐሜታ ።

የዘመኑ ሰው መላሱ ማለት ፡ ንግግሩ ፡ እንደ አህያ ጡት መንታ ፤ ወይም ሁለት ነው ። ከሁለቱም መካከል አንዱ የሰውን ፊት አይቶ ሰውን የሚያመሰግንበት ንግግር ሲሆን ፤ አንዱ ደግሞ ፡ በሌለበት ሰውን እያማ ፤ ወይም ጥሬ ሥጋውን እየበላ ስሙን የሚያጐድፍበት ነው ።

ለተሾመ ፡ ይሚገቱለታል ፤ በተሻረ ፡ ይመስክሩበታል ።

በዚህ ዓለም ላይ ሰው ሲጠላው አይቶ ፡ ምንም ያልበደለውን ሰው መጥላት ፡ እንዲሁም ሰው ሲወደው አይቶ ፡ ምንም ያላደረገለትን ሰው መውደድ የብዙ ሰዎች ልማድ ስለ ሆነ ፤ የተሾመ ሰው በክፉ ሲነሣ ፡ ሰዎች ይሚገቱለታል ፤ ያሳብቁለታል ፤ ሳይጠየቁም ፤

ዘሩን እየቁጠሩ ፤ ባለ ርስት ፡ ባለ ብዙ ወገን ፡ ያደር ጉታል ፤ ከሹመቱ በተሻረው ሰው ላይ ግን ፡ በሠራውና ባልሠራው ሥራ እየተሻሙ ያወሩበታል ፤ በተናገረውና ባልተናገረውም ነገር እየተደሰቱ ይመሰክሩበታል ፤ ማለት ነው ።

ያልገደለ ዘማች ፤ ያልወለደ አማች ።

ያልገደለ ዘማችና ያልወለደ አማች ሁለቱም አንድ ናቸው ፤ ምክንያቱም ፡ ለመዋጋት ተልኮ ፡ በጦር ሜዳ ላይ ጠላትን ያልገደለ ዘማች በግዳጁ የማይኮራ ፤ በማዕርግ የማያድግ ፡ ከማፈሩ የተነሣም ከጓደኞቹ እኩል የማይናገር ፤ የባልንጀሮቹ ደረት በሊሻን ሽልማት ሲንቄጠቄጥ ፤ የሱ ደረት ብቻ ሌጣ ሆኖ የሚታይ ስለ ሆነ ፤ እውነተኛ ዘማች እንደማይ ባል ፤ እንዲሁም ፡ ሚስትን አግብቶ ከመሰራረቅና ከመጠራጠር የሚያድን ፡ በባልና ሚስት መካከልም መተማመንና መተዛዘንን የሚያሳድር ልጅን ያልወለደ አማች በሚስቱ ዘመዶች ዘንድ አይከበርም ፤ « ነገ ሲቀር የሚቀር ነው » በማለትም እንደ ውጪ ሰው ስለሚቁጥሩት ፤ በቤተ ሰባቸው ጉዳዮች የተነሣ አይመካከሩትምና እውነተኛ አማች አይባልም ።

የምትኰነን ነፍስ ፡ ጎረቤት ያውቃታል ።

የምትኰነነውን ፡ ወይም የምትጸድቀውን ነፍስ አሳምሮ የሚያውቃት ጎረቤት የሆነ ሰው ብቻ ነው ፤

ምክንያቱም ፡ ጎረቤት ስሙ እንደሚያስረዳው ፤ ጥዋትም ፡ ማታም ፡ ቀንም ፡ ሌሊትም ፡ የማይለይ ፡ ጥሩም ሆነ መጥፎ ሥራ ቢሠራ ፤ በቅርብ ሆኖ የሚመለከት ጓደኛና የአጠገብ ዘበኛ ከመሆኑ የተነሣ ነው ።

የካህን አፋር ፡ የአህያ ዕውር ።

የታወረ አህያ ፡ በማንኛውም የጭነት ሥራ ሰውን ፡ ማገልገሉ ይቅርና ፤ ለራሱም ወደውጪ ወጥቶ ሣርን ግጦ ውሃን ጠጥቶ ፡ ወደ ቤቱ ለመመለስ እንደማይችል ሁሉ ፤ እንዲሁም አፋር የሆነ ካህን ወንጌልን ሰብኮ ፡ ያላመኑትን ለማሳመን ፡ መናፍቃንን ተከራክሮ ለማስረዳት ፡ ያመኑትንም በስብከቱና በምክሩ ለማረጋጋት ስለማይቻለው ፤ የካህን ዓይነ አፋር ልክ እንደ ዕውር አህያ ነው ።

የሌባ ሞኝ ፡ በጮተራ ሥር ይገኝ ።

በሰው እጅ ከተያዘ በኋላ ፤ በዱላ መደብደቡንና በእግር ብረት መታሠሩን የዘነጋ የሌባ ሞኝ ቢሰርቅ ፤ የያዘውን ይዞ ባይሰርቅ ፤ ባዶ እጁን እግሬ አውጭኝ ፡ ብሎ እንደ ማምለጥ ፡ እውነተኛ ሰው ይመስል ፤ በጮተራ ሥር ይገኛል ።

የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ ።

ስለ ሌባ የሚከራከረው ፡ ሌባ ነው ። የሚጠቁምና የሚመራውም ሌባ ነውና ፤ ሌባው ተይዞ ከተመረመረ በኋላ ፤ እነዚህም ሁሉ ተለቃቅመውና አብረው በሚገባ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ማድረግ ይገባል ማለት ነው ።

የደመና ውሃ ጥምና ፡ የናት በደል ፡ አይታወቅም ።

ደመናማ ዕለት ፡ የቀኑ አየር በጣም ቀዝቃዛና ብርዳም ስለሆነ ፤ «ወሃ ጠማኝ ፤ » የሚል ሰው ቢኖር ፤ ከደረሰበት ሰው በስተቀር ፤ በብዙ ሰዎች ዘንድ ፡ ጮልቶ አይታወቅም ። እንዲሁም እናት ስትባል ፤ በጠቅላላ ርኅሩኅና በጣም አዛኝ በመሆኗ «እናቴ በደለችኝ » የሚል ሰው ቢኖር ፤ ከተነካ ሰው በስተቀር ፤ ብዙዎቹን ለማመን ያስቸግራቸዋል ።

ዕኑ ወዳጅ ፡ ዕኑ ጠላት ይሆናል ።

ዕኑ ወዳጅን በኧ ምክንያት የተጣሉት ወይም ያስቀየሙት እንደ ሆን ፤ የነበረውን ጥብቅ ወዳጅነት

መልካም ውለታውንና ታማኝነቱን እያሰላሰለ በጣም ስለሚቀየም ፤ ብርቱ ጠላት ይሆናል ። ቢፈልግም ወዳጅ የነበረውን ሰው በቀላሉ ለማጥፋት አይሳነውም ፤ ምክንያቱም በወዳጁ ቤት ፡ ገቢና ወጪ ፡ በዱና ጠጪ አብሮ መካሪና ተቆርቋሪ ፡ ስለ ነበረ ፤ ያለፈው ያሁኑና የወደፊት ምሥጢር ከርሱ ዘንድ የማይደበቅ ውስጠ ዓወቅ ከመሆኑ የተነሣ ነው ።

ዳኛ ፡ ቢያጋድል ፡ በዳኛ ፤ አህያ ቢያጋድል ፤
በመጫኛ ።

አህያ በመንገድ ፡ ወይም በአካኼድ ምክንያት ጭነቱን ቢያጋድል ፤ የጭነቱን ሚዛን በመጫኛ ጠበቅ ተደርጎ እንደሚስተካከል ሁሉ ፤ እንዲሁም ዳኛ ፡ በግል ጥቅም ተደልሎ ፍርዱን ቢአዳላ ፤ «ይግባኝ» ብሎ ፍርዱን በሰበር ዳኛ ለማስገልበጥ ይቻላል ።

ጠላት ፡ ይቀባል ጥላት ።

ጥላት ነጭ ልብስን አበላሽቶ ሲታይ ፤ ልብሱንና ለባሹን ሰው ማስጠላቱ የታወቀ ነው ፤ ስለዚህ «ጠላት ይቀባል ጥላት » ማለትም ሰብዓዊ ሕሊናው የማይወቅሰው ጠላት የሚጠላውንና የሚመቀኘውን ሰው በሰው ዘንድ ለማስጠላት ያልሠራውን አደረገ ፤

ያላለውን ተናገረ ፤ ያባት የናቱ ዘር እንዲህ እንዲህ ነው ፤ ያባት የናቱ ሥራቸውና ጠባያቸውም እንደ ዚህ ያለ ነበረ ፤ እያለ ያወራበታል ፤ ማለት ነው ።

የነገር ወጡ ፡ ማዳመጡ ።

የነገር ወጡ ፡ በደንብ ማዳመጡ ነው ፤ ማለት ፤ የሚነገረውን ነገር በውል ማዳመጥ ፡ የነገርን ጫፍ ይዞ ፡ ከመጣላትና ከመሳሳት ያድናል ማለት ነው ፤ ነገር ግን ፡ እንጀራ ፡ ያለ ወጥ ፡ የተፈለገውን ያህል እን ደማይበላ ፤ እንዲሁም በትክክል ያልተደመጠ ነገር ፡ እንደ ባቢሎን ግንበኞች ቋንቋ ፡ ያበጣብጣል እንጂ ፤ የታሰበውን ያህል አይጠቅምም ።

ይሉሽን ፡ በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ።

ማንም ሰው ፡ የሠራውን ነውር ራሱ ባያጣውም እንኳ ፤ ከሰው አፍ በግልጽ ካልሰማው በስተቀር ፤ ብዙ ሰው ዐውቆት እሱ በሌለበት እያማውና እየሳ ቀበት በፊቱ ዝም ቢለው ፤ «አልታወቀብኝም » እያለ ራሱን ማጽናናት የተለመደ በመሆኑ ነው እንጂ ፤ ሰዎች የሚሉሽን ሐሜታ እንደኛው በሰማሽው ኖሮ ፤ በሐፍረት ኩምችች ከማለትሽ የተነሣ ፡ ትደበቂ ነበር እንጂ ፤ ብዙ ገበያተኛ ወደ ሚውልበት ወደ ገበያ ባልወጣሽ ነበር ።

ጊዜም ቢሆን ፥ ከፍተኛ እንጂ ዝቅተኛ ሆኖ አያውቅም ፤ ስለዚህ ፥ ሁሉም እኩል ጥሩ ዕቃ በደኅና ዋጋ ፥ ቄንጆና ጠባየ መልካም ሚስት በጥቂት ወጪ ብዙ ሀብት በአ ነስተኛ ድካም ለማግኘት ይፈልጋል ፤ ነገር ግን ቂጣን መብላት በመናቅ የነጭ ጤፍ እንጀራን በመልካም የዶሮ ወጥ ለመብላት ሲወዱና ፤ ሲጠብቁ ፤ አልቆ ፥ ወይም ጠፍቶ ፥ የጠሉትን ቂጣ የሚበሉበት ጊዜ ስለ ሚያጋጥም ፤ ይህ ምሳሌ ሲመሰል ይኖራል ።

የነሐሴ ወሃ ፥ ጥሩ ነው ፤ የሚጠጣው የለም ።
የድኻ ምክር ፍሬ ነው ፤ የሚሰማው የለም ።

የሰኔና የሐምሌ ዝናብ ጐርፍ ፤ ድፍርሱን ውሃ ከቄ ሻሻው ጋራ ከምድር ላይና ከወንዞች ውስጥ ጥርግርግ አርጎ ስለሚወስደው ፤ የነሐሴ ውሃ እንደ ተኩላ ብር በጣም የጠራ ነው ፤ ነገር ግን ውሃው ፥ በጥራቱ የሚያ ስጐመጅ ቢሆንም እንኳ ፤ ወሩ ቀዝቃዛ በመሆኑ የሚ ጠጣው ሰው በጣም ጥቂት ነው ። እንዲሁም ፥ ድኻ የሚናገረው ምክር በሥራ ላይ ሊውል የሚገባው ፍሬ ነገር ነው ፤ ይሁን እንጂ ፥ በማስተዋል የሚያዳምጠው የለም ፤ ምክንያቱም ፥ ሰው ግብዝ ከመሆኑ የተነሣ ፥ ልቡ የነገሩን ጠቃሚነት አሳምሮ ሲያውቀው ፤ የሰውዮውን ድኽነት ብቻ በመመልከት ስለሚንቀው ነው ።

ያምራል ብሎ ከተናገሩት ፥ ይከፋል ብሎ የተዉት ።

ያምራል ብሎ ከተናገሩት ንግግር ይልቅ ፥ ይከ ፋል ብሎ የተውት ሐሳብ ይበልጣል ፤ ምክንያቱም ከተናገሩ ዘንድ አድማጮችን የሚያስቀይሙ ዓረፍተ ነገሮችና ቃሎች ከአፍ ስለሚያመልጡ ሲሆን ፤ ዝም ካሉ ግን በልብ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ለማወቅ ስለ ማይቻል ነው ።

የወጣት ሹም ፥ የጎዳር ጉም ፥ ሀገር ይደረግም ።

የወጣት ሹምና የጎዳር ጉም ፥ አንድ ናቸው ፤ ስለ ምን ፥- ቢሉ የጎዳር ወር በብዙዎቹ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች የደረሰ እህል የሚሰበሰብበት የመከር ጊዜ ስለ ሆነ፤የዚሁ ወር ጉም ፥ ወደ ደመናነት ተለውጦ ዝናብ ቢጥል ፤ ዝናቡ ከአንበጣ ይበልጥ አዝመራን ስለሚያበላሽ ነው ። እን ዲሁም አንዳንድ የወጣት ሹም አእምሮው ያልበሰለ እልሁ ያልሰከነ ፥ ብዙ ትምህርቶችን ከመከራና ከዕድሜ ትምህርት ቤት ያልሰበሰበ ፥ ነገርን ጠልቆ የማያመዛ ዝን ፥ ትዕግሥቱ ያነሰ ፥ ቂጣው የበዛ ፥ ከመሆኑ የተነሣ፥ የተሾመበትን አገር እንደ መብራት እልም አርጎ የሚያ ጠፋ ስለሆነ ነው ።

የወደዱትን ሲያጡ ፤ የጠሉትን ይቀላውጡ ።

ሰው ፥ ምንም እንኳ የዕድሉ ደረጃ ዝቅተኛ ፥ መካ ከለኛና ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ ፤ የሰው ፍላጎት ፥ ምን

ከጠላት ስሞሽ ፡ የወዳጅ ንክሻ ።

ከጠላት ስሞሽ ፡ የወዳጅ ንክሻ ይሻላል ፤ምክን ያቱም ጠላት ሲስም ከልቡ ውስጥ እየዛተ ነው ። ወይም ለመከራ አሳልፎ ለመስጠት ፈላጊውን እየ ጠቆመ ነው ፤ የወዳጅ ንክሻ ግን ለጨዋታ እንጂ ፤ ከቂም በቀል መንጭቶ የተሰነዘረ ማጥቂያ ስላልሆነ ፤ ጭካኔ የሌለበት በመሆኑ ብቻ ነው ።

በናት ላይ አክስት ፤ በሰንበት ላይ ደብረ - ዘይት ።

በናት ላይ አክስትን ማግኘት ፡ በክርስቲያን ሃይ ማኖት በየሳምንቱ እየተከበረ በሚውለው የሰንበት ቀን ላይ «ደብረ - ዘይት » የሚባለው ታላቅ የዓመት በዓል ተደርቦ እንደሚውልበት ቀን መሆን መታደል ነው ።

የሚያልፍ ዝናብ ፡ አይምታህ ፤ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምኽ ።

ልብስህ በስብሶ አንተንም በርዶህ በበሽታ ላይ እንዳትወድቅ ፡ ዝናቡ ዘንቦ እስቲያባራ ድረስ ፤ በትዕ ግሥት አንዱጋ ተጠለል እንጂ ፤ ከመቸኰልህ የተነሣ ፈጥኖ የሚያልፍ ዝናብ እንዳይመታህ ፡ ተጠንቀቅ ። እንዲሁም ያንን የመሰለ ጐልማሳ እንደዚህ ሆኖ

በማርጀቱና እቤትም ውሎ እንደሰባራ ዕቃ በመናቁ እያሰበ ስለሚበሳጭ ፤ ለመመረቅም ሆነ ይቅርታን ለማድረግ ጊዜ የለውምና ፤ ከቻልህ ምርቃቱን ለመ ቀበል ፤ ርዳታ አድርግለት እንጂ ፤ ቆራጥ የሆነ እር ግማኑ እንዳይደርስብህ የመሞቱን ሰዓት ብቻ የሚጠ ባበቀውን ሽማግሌ ከማስቀየም መራቅ አለብህ ።

ካላዩ ፤ አይነድ ፡ ካልሰሙ ፤ አይቆጭ ።

ጥሩ ዕድል ፡ ሲያመልጥ ፤ ወይም ክፉ ሥራ ሲፈ ጸም ፤ ዓይን በዓይን ካላዩ ፤ አይነድም ፤ ወይም መና ደድ የለም ። እንደዚሁም ፡ በሌሉበት ቢታሙና ፤ ቢቦጨቁ ፤ ቢሰደቡና ቢናቁ ፤ እንዳጋጣሚ ካላዳመጡ ወይም ከሰው አፍ በወሬ ካልሰሙ በስተቀር ፤ ምንም አይቆጭም ።

የልጅ መጥፎ ዲቃላ ፤ የእህል መጥፎ ባቄላ ፤ የልብስ መጥፎ ነጠላ ።

ዲቃላ ማለት ፡ ከሕግ ውጪ የተወለደ ልጅ ማለት ሲሆን ፤ ከተወለደ በኋላም ፤ ተገቢ አስተዳደግ የሚጐድለው ፡ የሱም ጠንቅ ፡ ገና ያላገቡትን ፡ የትዳር ጓደኛን የሚያሳጣ ፡ ተጋብተው ደኅና የተቀመጡትን ባልና ሚስት የሚያፋታ ፡ ስለሆነ ፤ የልጅ መጥፎ

ዲቃላ ነው ። ባቄላ ፣ ጥሬ እህል ከሚባሉት እህሎች ውስጥ አንዱ ነው ፤ ይሁን እንጂ ፣ ብቻውን ቢበሉት ፤ ሰውነትን የማይደግፍ ፣ ከመሆኑም በላይ ሆድን የሚቀ በትት ፣ በእንጀራነት ፣ በቂጣነትና በጠላነት የማያገ ለግል ስለሆነ ፤ የእህል መጥፎ ባቄላ ነው ። ነጠላ ፣ ቢለ ብሱት ሰውነትን ያማያሞቅ ፣ ከብርድ የማያድን ፣ ለሚ ደርቡት ግርማና ክብደት የማይሰጥ ፣ በመሆኑ ፣ የል ብስ መጥፎ ነጠላ ነው ።

የልጅ ነገር ፪ ፍሬ ፤አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ ።

የልጅ ነገር ፣ ወይም ሥራ ፪ ፍሬዎች ሲሆኑ ፤ ከነርሱም ፣ አንዱ ብስል ፣ አንዱ ፣ ጥሬ ናቸው ። ከነዚህም ውስጥ «አንዱ ብስል» የተባለው ፣ አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደ ዐዋቂ ሰው ቁም ነገርን የሚያናግ ረው የሰብዓዊነቱ ጠባይ ነው ። «አንዱ ጥሬ» የተባ ለውም ፣ ጥፋት ፣ ዝላይና ጨዋታ ፣ የማይረባ ሐሳብ ፣ ጥቅምና ጉዳትን አለማመዛዘን ፣ ይሉኝታ ማጣት ፣ ቅጣ ትንና ምክርን ፈጥኖ መርሳት ፣ የተባሉትና የሚመ ስሏቸውም ሥራዎች በልጁ ላይ እንዲገኙበት የሚ ያደርግ የሕፃንነቱ ጠባይ ነው ።

ውሎ ውሎ ከቤት ፤ ኖሮ ኖሮ ከመሬት ።

በየቀኑ ለአስፈላጊው ጉዳይ የትም ውሎ ውሎ ሲመሽ ለአዳር ወደ ቤት መግባት ግዴታ ነው ። እን

ዲሁም በዚህ ዓለም ለጥቂት ዓመታት ብቻ የሚረባ ውንና የማይረባውን ሥራ እየሠሩ በሕይወት ሥጋ ኖሮ ኖሮ ፣ ተመልሶ ወደ መሬት ገብቶ መቀበር የማይ ቀር ዕዳ ነው ።

ራስ ሲመለጥ ፤ ነገር ሲያመልጥ ፤ አይታወቅም ።

የሰው ራስ ፀጉሩን ተመልጦ ከመታየቱ በስተቀር ፣ ገና ሲመለጥ ሳለ ፤ ምንም እንደማይታወቅ ሁሉ ፤ እንዲሁም እንደ ወንጀለኛ በልብ ውስጥ ሊታሠር የሚገባው ነገር ፣ ወይም ንግግር ከተናጋሪው አፍ ድንገት ሲያመልጥ ከቶ አይታወቅም ።

አንድ በሬ ስቦ ፤ አንድ ሰው አስቦ ።

አንድ በሬ ብቻውን ሞፈርንና ሞፈር የያዛቸውን መሣሪያዎች ሁሉ ስቦና መሬትንም አርሶ የእርሻውን ሥራ ሊያከናውን እንደማይችል ፤ እንዲሁም በዚህ ዓለም ኑሮ ሐሳብንና ሥራን ብዙ ሰዎች ካልተከፋፈሉአቸው በስተቀር ፤ አንድ ሰው ብቻ ለብዙ ሰዎች አስቦና ሠርቶ ለመኖር አይችልም ።

ጌታውንና በሽታውን የሚንቅ ፣ እያደር ይወድቅ ።

በአንዳንድ ምክንያት የተነሣ ፣ የበላዩን የሚን ቅና ለበላዩም ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ከመፈጸም

ችላ የሚል ሰው ፡ የበላዩ ይቀየመውና ፡ ከሱ በኋላ ተቀጥረው የሚሠሩት ሁሉ ሲሾሙና ሲሸለሙ ፤ የማዕርግና የደመወዝ እድገትንም ሲያገኙ ፤ እርሱ ብቻ እያደር ውዳቂና ተስፋ ያጣ ሆኖ ይቀራል ። እንዲሁም ምናልባት ወደፊት ድንገት ይጠፋልኝ ይሆናል ፤ በሚል ተስፋ ተማምኖ በሽታውን የሚንቅና የሚደብቅ ፡ ለጤንነቱም ፡ ሊአደርግ የሚገባውን ክብክብ ችላ የሚል ሰው ፡ በጊዜው የታከሙት ሁሉ ጤናቸውን ሲያገኙ ፣ በፊት የናቀውና የደበቀው ሕመሙ ፡ ሥር ሰዶ ፤ እርሱን ብቻ ከሰውነት ውጪ ስለሚያደርገው ፤ እያደር የመዳን ተስፋ የሌለው ሆኖ በሞት እጅ ይወድቃል ።

ካለ መናገር ፡ ደጃዝማችነት ይቀራል ።

እውነተኛ ተመልካችና መልካም ውለታ መላሽ በሌለበት ቦታ ሁሉ ፡ ካልተናገሩና ካልተጨቃጨቁ ፣ ወይም በገንዘብ ጉቦና በዘመድ ደጅ ካልጠኑ በስተቀር ፣ ደጃዝማችነት ፤ የቀራል ። የደመወዝ ጭማሪም ይታገሳል እንጂ ፤ ይገባዋል ፤ በሚለው ቁና አስተያየት ከቶ አይገኝም ።

ክፍል ፰ ፡

የምሳሌዎች አጭር አፈታት ፤

ከአማርኛ ምሳሌዎቻችን ውስጥ ፤ ብዙ የምሥጢር ተመሳሳዮች ፡ ወይም ምሥጢራቸው ያው አንድ የሆነ ምሳሌዎች ፡ ስለሚገኙ ፤ አንዱን ምሳሌ በተመሳሳዩ ምሳሌ መፍታት ፤ ወይም ምሳሌዎቹን እርስ በራሳቸው ማተረጓጎም « የምሳሌዎች አጭር አፈታት » ይባላል ።

ለምሳሌ ፡

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በግ ! ባልበላሽ ፤ ችበዪኝ !
እሳት ፡ ቢያንቀላፋ ፤ ገለባ ፤ ጐበኘው ።
ዶሮ ፤ ጭራ ጭራ ፤ ታወጣለች ካራ ።
አህያ ፤ ወደ ዥብ ለቅሶ ሄደች ።
ገዳይ ቢአረፍድ ፤ ሟች ፤ ይገሰግሳል ።
አይጥ ፤ ለሞትዋ የድመትን አፍንጫ ታሸታለች ።
እሳት ፤ ቢተኛ ፤ ገለባን ሰደደ ገበኛ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በቅሎ አጐቴ አጐቴ ይላል ፤ ፈረስ ግን ግድ የለውም ።
ግዣኝ ብለው ፤ ሊሸጠኝ አሰበ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እሾህ ፡ አጣሪውን ፤ ነገር ፤ ሠሪውን ።
ስለት ፡ ድጉሱን ፤ ደባ ፡ ራሱን ።
በቅሎ ፡ ለኮዋን በጠሰች ፡ በራስዋ አሳጠረች ።

እርስ በራሳቸው ፡ የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በመልክ ቢጠፉ ፤ በስም ይደጋፉ ።
በጦሩ ቅብጭ ፡ በጠላው ቁጭ ።
ከእንጀራው የለሽ ፡ ከወጡ የለሽ ፡ ከጠላው የለሽ
እንዲያው በላይነሽ!

እርስ በራሳቸው ፤ የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ራስ ፡ ሳይጠና ፤ ጉተና ።
ዓባይ ፤ ማደሪያ የለው ፤ ግንድ ይዞ ይጓዛል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በሰበቡ መምሬ ተሳቡ ።
በልጅ አመካኝቶ ፡ ይበሏል አንጉቶ ።
ስሙ በካህን በላተኛው መሃይምን ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የራስዋን አበሳ በሰው ላይ አብሳ ።
የአብዮን እከክ ወደ እምዬ ላከክ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ብርሌ ከነቃ ፤ አይሆንም ዕቃ ።
ዲያቆን ከዘራሉ ፤ ፍየል ከቀዘነ ፤ አይድንም ።
የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ ፤ አያርፍም ።
የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ለቀባሪ አረዱት ።
ምጥ ለናትዋ አስተማረች ።
ለአንበሳ አይመትሩ ፤ ለብልህ አይነግሩ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የግፍ ግፍ በዕንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ ።
እምበላው ሳጣ ፤ ልጄ ፤ ጥርስ አወጣ ።
በቦሀ ላይ ቆረቆር ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ቱናዳጅ እንጂ ፤ አናዳጅ አይሞትም ።
የተከሩ ተደሩ ።

እርስ በርሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የማያድን ጋሻ ጐን ያሰብራል ።
አገባሻለሁ ያለሽ ላያገባሽ ክባልሽ ሆድ አትባባሽ ።
የአህያ ባል ከሾብ አያስጥል ።
ከእጅ አይሻል ዶማ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ።
የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ ።
ከዳቦ የተገኘውን ወጥ አብረህ ግመጥ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ተልባ ቢንጫጫ ፤ ባንድ መቁጫ ።
የሹሮ ድንፋታ እንጀራ ፤ እስቲቀርብ ድረስ ነው ።
ዝንብ ቢሰበሰብ ፤ ምንችት አይከፍትም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አለባለቤቱ አይነድም እሳቱ ።
ባለቤት ካልጮኸ ፤ ጐረቤት አይረዳም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አለባብሶ ቢያርሱ ፤ በአረም ይመለሱ ።
ተንጋሎ ቢተፉ ፤ ተመልሶ ካፉ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ላም አለኝ በሰማይ ፤ ወተትዋንም አላይ ።
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ማን ያውቃል አገር ። ምን ያጠብቃል ማገር ።
የምትኰንን ነፍስ ጐረቤት ያውቃታል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

መናገር ብር ነው ፤ ዝማታ ወርቅ ነው ።
ዝም ፤ አይነቅዝም ።

እርስ በርሳቸው የሚተረጓጐሙ ምላሌዎች ፤

የነገር ወጡ ማዳመጡ ።
ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የሆድ ብልሃት የጋን መብራት ።
ካልታረደ ፤ አይታይ ስባቱ ፤ ካልተናገረ ፤ አይታደ ብልሐቱ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው ።
ረሾም ጦር ባይወጉበት ፤ ያስፈራሩበት ።

ሆድን በጐመን ቢደልሉት ፤ ጉልበት በዳገት ይለ
ግማል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ዥብ እንደ አገሩ ይጮኻል ።
እንደ ንጉሡ አጐንብሱ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አይጠቅም ጠላ ባልና ሚስትን አጣላ ።
የሚያልፍ ነገር የማያልፈውን ስም ያጠፋል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አዘዞ አንድም ተናዞ አንድም ስንቅ ይዞ ።
ወዴት ትኼዳለህ ፡- ወደ በለሳ ። ሰሌን የለህምሳ ፡-

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አሞራን ሲበሉ ፤ ስሙን ዥግራ ይሉ ።
አያ ዥቦ ! ሳታመካኝ ብላኝ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እሳት ቢዳፈን ፤ የጠፋ ይመስላል ።
ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አንድ ግንድ ለሺ አይከብድ ።

ሃምሳ ሎሚ ለ፯ ሰው ጌጡ ነው ፤ ለ፩ ሰው ግን
ሸክሙ ነው ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ዥብ ካኼደ ፤ ውሻ ጮኸ ።
ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ደንጊያ መንከስ ።
ዝናብ ሲያባራ ፤ወደ ዋሻ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ጥርስና ከንፈር ተደጋግፎ ያምር ።
ድር ቢያብር ፤ አንበሳን ያሥር ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አንበሳ ሲያረጅ ፤ የዝንቦች መጫወቻ ይሆናል ።
ጨሌ ሲያረጅ ፤ መጋረጃ ይሆናል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ያልጠረጠረ ተመነጠረ ።
ያላሰበ ተመነደበ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ፊት የተናገረውን ሰው ይጠላው ፤ ፊት የደረሰውን
ወፍ ይበላው ።
ተናካሽ ውሻ የዥብ መቋደሻ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ይገርማል ! አህያና ሸጉብ አብሮ ይከርማል !
በሬ ካራጁ ጋራ ይኼዳል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል ።
ለኻያጅ የለውም ወዳጅ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ሁለት ባላ ትኳል ፤ አንዱ ሲነቀል ፤ ባንዱ ተንጠልጠል ።
ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ ፡ አትሞትም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የላጪን ልጅ ቅማል በላው ።
የዓባይ ልጅ ውሃ ጠማው ።
መርፌ የራስዋን ቀዳዳ ሳታይ ፤ ብዙ ጨርቅ ትጠቅ ማለች ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ፈረስ ቢያነክስ ፤ አህያ ተነሱስ ።
አይጥ በበላ ፤ ዳዋ ተመታ ።
አህያውን ፈርዶ ዳውላውን ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አተርፍ ባይ አጉዳይ ።

ዓሣ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ። የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ።
አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል ።
ራስዋን ሹርባ ልትሠራ ኼዳ ፀጉሯን ተነጭታ መጣች ።
የቆጡን አወርድ ብላ የብብትዋን ጣለች ።
ተኩላ እንደ አንበሳ እጮኻለሁ ብላ ተተረተረች ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አፍ ሥራ ሲፈታ ፤ ወዳጁን ያማል ።
ሥራ ከመፍታት ልጇን ላፋታት ።
ዕውር ሲቀናጣ ፡ ዘንጉን ወርውሮ ይፈልጋል ።
ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀድዶ ይሰፋል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እባብ ለባብ ይተያያሉ ካብ ለካብ ።
ብልጥ ለብልጥ ይተያያሉ ፤ ውስጥ ለውስጥ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ዓይን ካላዩበት ፤ ግንባር ነው ።
አህያ ካልተጫነ ፤ አሳማ ነው ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አልሞት ባይ ተጋዳይ ።
ሸጉብ ከሚበላኝ ፤ ሸጉብ ቢልቼ ልቀደስ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እርሾው ቢያምር ፤ ዳቦው ያምር ።
ቅርንጫፉ እንደ ዛፉ ።
የማሽላ ዘር ከነ አገዳው ቸር ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እሚሉሽን በሰማሽ ፤ ገበያ ባልወጣሽ ።
መርፌ የምትሾልክበትን እንጂ ፤ የሚከተላትን ክር አታይም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ ።
እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ ።
አያ ጅቦ ! እንኳን ድን በልተህ ድሮም ጪኺ ነህ !

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በአንድ ወናፍ ሁለት አፍ ።
በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አብ ሲነካ ፤ ወልድ ይነካ ።
አፍንጫ ሲመታ ፤ ዓይን ያለቅሳል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አህያ በሞተች ባመቱ ኩር ኩር !
ዓምና የሞተውን ጥጃ ስደዱ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አረምን መንቀል ሥር ሳይሰድ ነው ።
ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቈረጠምም ።
ልጅን መቅጣት በጡት ።
ሳይቃጠል ፤ በቅጠል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እህል ሲገኝ ፤ ወፍጮ ይደንዛል ።
ድኻና ገበያ ሳይስማሙ ይኖራሉ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ጌታውን የተማመነ ውሻ ሰንጋ ሲታረድ ፡ ወንዝ ይውረድ ።
ጠባቂ ያላት በግ ላትዋ እደጅ ያድራል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እህል ላበደረ አፈር ፤ ወርቅ ላበደረ ጠጠር ።
ባጐረስኩ ፤ እጄን ተነከስኩ ።
ያሳደግኩት ውሻ ነከሰኝ ፤ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
በርበሬ በገዛ እጅ ገዝቶ ይፈጭል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እጅና አፍ አይተጣጡም ።
ዘመድ ከዘመዱ ፤ አህያ ካመዱ ።
ዘር ከልጓም ይስባል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

እርሻ ሲሉ ፤ ሞፈር ቄረጣ ።
ሠርገኛ መጣ ፤ በርበሬ ቀንጥሱ ።
ጦር ሲመጣ ፤ ዛብያ ቄረጣ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ከእሾህ ወጥቶ ወደ ጋሬጣ ።
ከዥጉብ ጐሬ ወጥቶ ወደ ዥጉብ ዋሻ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አላዋቂ ተራች የራሱን አመልካች ።
ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል ።
ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽንብራ ።
እኔም ሌባ ፤ አንተም ሌባ ፤ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ ።-

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ ።
የለመደ መደመደ ።
በፋሲካ የተገዛች ባሪያ ሁል ጊዜ ፋሲካ ይመስላታል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር ።
ውሎ ውሎ ከቤት ፤ ኖሮ ኖሮ ከመሬት ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ራት የሌለው ቄስ እንደ ልቡ አይቀድስ ።
ከሆዱ ላይ ቅሉል ያለበት ውሻ እንደ ልቡ አይጮህም ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ወጌሻ ፡ ሲበዛ ፤ በሽተኛ ይሞታል ።
ሴት ፡ ሲበዛ ፤ ጐመን ጠነዛ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አንድ ቀን ቢሰቱ ፤ ዓመት ይጸጸቱ ።
ያንድ ቀን መዘዝ ያለ አንድ ዓመት አይመዘዝ !
አንድ ቀን ስትሰርቅ ካዩአት ፤ ብትቄርብም አያምኗት ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

አህያ ላህያ ቢራገጥ ፤ ጥርስ አይሳበርም ።
የዘመድ ጥል የሥጋ ትል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ባባቱ ከተማ ፡ ልጁ ተቀማ ።
ዓሣ ፡ በወንዙ ይታረዳል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ዓይን አፋር ልጃገረድ ከወንድምዋ ታረግዛለች ።
በየዋህ ቤት እንግዳ ይዋኝበታል ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ቀጥተኛ ሲታጣ ይመለመላል ጐባጣ ።
የወደዱትን ሲያጡ ፤ የናቁትን ይቀላውጡ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም ።
የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ ፤ አንዱ ብስል ፤ አንዱ ጥሬ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ወድደሽ ከተደፋሽ ፤ ቢረግጡሽም አይክፉሽ !
በመረጡት ዳኛ ቢረቱ ፤ በቄረጡት በትር ቢመቱ ፤
በማን ያጉመተምቱ ።

አዎን ፡ ብሎ የተረታ ባላጋራ ከሥሩ እንደ ተነቀለ
ወይራ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደስ ።
ይበጃል ያሉት መድኃኒት ዓይን አጠፋ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የሸዠብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ።
የቸኰለ ፤ አፍስሶ ለቀመ ።
ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ።
ፈጥኖ መስጠት ኻላ ለመጸጸት ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

የፉክክር ቤት ፡ ሳይዘጋ ፤ ያድራል ።
የጋራ ወንጋራ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ ።
ምንም ቢከፋ ፤ ዘመድ ፤ ምንም ቢጠብ ፤ መንገድ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ከክፉ ባለ ዕዳ የጐመን ዘር ተቀበል ።
ከነገሩ ጦም ይደሩ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ግማሹን ተላጭታ ግማሹን ተቀብታ ።
ከወገብ በላይ ታቦት ፤ ከወገብ በታች ጣዖት ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

በሽታውንና አለቃውን የሚንቅ እያደር ይወድቅ ።
ከበላዩ የተጋፋ እጅግም አይፋፋ ።
መንፈራገጥ ለመላላጥ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌዎች ፤

ከአነጋገር ይፈረዳል ፤ ከአያያዝ ይቀደዳል ።
በአፍ ይጠፉ ፤ በለፈለፉ ።
ዕውርን ቢፈርዱ ፤ ዕውርን ይወልዱ ።

እርስ በራሳቸው የሚተረጓጐሙ ምሳሌች ፤

ባጠፋ ወታደር ፤ ይክሳል ባላገር ።
ድኻ ተበድሎ ፤ ማሩኝ ይላል ቶሎ ።

ክፍል ፱ ፡

የግሥ ዖታና ቊጥር በምሳሌዎች ፤

ከአማርኛ ምሳሌዎች መካከል የግሦችን ዖታና ቊጥር እያፋለሱ ፡ የሚነገሩ ምሳሌዎች ይገኛሉ ። እነርሱም ከዚህ በሚከተሉት መሥመሮች ላይ የተጻፉትና የሚመሰሉዋቸውም ናቸው ።

ለምሳሌ ፡

ምሳሌዎቹ ፡	ግሦቹ ፡
ፈረና ንፉግ እያደር ይቆጨዋል ።	(እያደር ይቆጫቸዋል ።)
ዕብድና ዘበናይ የልቡን ይናገራል ።	(የልባቸውን ይናገራሉ)
እሳትና ድኻ ሲነካኩት አይወድም ።	(ሲነካኩዋቸው አይወዱም)
ባዳና ጨለማ አንድ ነው ።	(ባዳና ጨማ አንድ ናቸው)
ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው ።	(ማስፈራሪያ ናቸው)
ውሻና ቊን ሳይጠሩት ይመጣል ።	(ሳይጠሩዋቸው ይመጣሉ)

ምሳሌዎቹ ፡	ግሦቹ ፡
ዕድሜና መስተዋት አይ ጠገብም ።	(አይጠገቡም ።)
አባይና ስንቅ ፣ እያደር ይቀላል ።	(እያደር ይቀላሉ ።)
አፍና ቅብቅብ ሁልጊዜ አያበላም ።	(ሁልጊዜ አያበሉም ።)
አማችና ጋሻ ካልሰጉ ዱት አይሆንም ።	(ካልሰጉዱአቸው አይሆኑም ።)
ሞኝና ውሃ ወደ ወሰዱት ይኼዳል ።	(ወደ ወሰዱአቸው ይሂዳሉ)
ሆድና ግንባር አይሸሸግም።	(አይሸሸጉም ።)
ሳይጣሉት የተጣላ ሲርብ ያበላ አይረሳም ።	(አይረሱሙ ።)
ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይቀምስ ።	(ያቀረቡላቸውን ይቀምሳሉ ።)
ላም አለኝ በሰማይ ወተ ቷዋንም አላይ ።	(ላም አለችኝ በሰማይ ።)
ጥርስና ከንፈር ተደጋግፎ ያምር ።	(ተደጋግፈው ያምራሉ።)
ይገርማል ! አህያና ዥብ አብሮ ይከርማል !	(አብረው ይከርማሉ ።)

ምሳሌዎቹ ፡	ግሦቹ ፡
ዳኛ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት አንድ ነው	(አንድ ናቸው ።)
የወጣት ሹም የጎዳር ጉ ጉም አገር ይደረግም ።	(አገር ይደረግሙ ።)
የወደደና ያበደ አንድ ነው ።	(አንድ ናቸው ።)
የደመና ውሃ ጥምና የናት በደል አይታወቅም ።	(አይታወቁም ።)
እውነትና ንጋት ፣ እያደር ይገለጣል ።	(እያደር ይገለጣሉ ።)
ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራል ።	(በራሳቸው ያወራሉ ።)
መከራና አፈር ቢዝቁት አያልቅም ።	(ቢዝቁአቸው አያልቁም)
ደፋርና ጪስ መውጫ አያጣም ።	(መውጫ አያጡም ።)
ሕልምና ጉም አይጨበጥም ።	(አይጨበጡም ።)
ዱባና ቅል ያው አንድ ይመስል ፤ አገልግሎቱ ለየቅል ።	(አንድ ይመስላሉ) (አልግሎታቸው ።)

ክፍል ፲ ፡

የምሳሌዎች አሰካክ ፤

አብዛኞቹ ምሳሌዎች የአሰካካቸው ወይም የአነጋገራቸው ሁኔታ ልክ እንደ ግጥም ዓረፍተ ነገር ስለሆነ ፡ በግጥም ዓረፍተ ነገር ላይ ውስጠ ታዋቂዎች የሚሆኑት ኹሉ በምሳሌዎችም ላይ ውስጠ ቀሪዎች ይኾናሉ ።

ለምሳሌ ፡

ምሳሌዎቹ ፡	ውስጠ ቀሪዎቻቸው ፡
አይመጣምን ፡ ትተሽ ይመጣልን ፤ በያዝሽ !	አይመጣም ማለትን ትተሽ ይመጣል ማለትን በያዝሽ ።
ከመነሱሴ ቤት ስስት ከሸማኔ ቤት ቁጢት ።	አይጠፋም ።
የጋራ ወንጋራ ።	ነው ።
የነገር ወጡ ማዳመጡ ።	ነው ።
ዳዊትና ሚስት በብብት። ከአጣቢ አደራቂ ፤	መያዝ ነው ።
ካዋቂ ጠያቂ ።	ይሻላል ፤ ይበልጣል ።

ምሳሌዎቹ ፡	ውስጠ ቀሪዎቻቸው ፡
ፈረስና ጥሬ ፡ ሴትና ወሬ ።	ይዋደዳሉ ።
የሹም ከርፋፋ ፡ አገር ያጠፋ ።	(ያጠፋል ።)
ስለት ፡ ድጉሱን ፤ ደባ ራሱን ።	ይቁርጣል ፤ ያጠፋል ።
እገድል ያለ መጋኛ ፤ እበላ ያለ ዳኛ ።	አንድ ናቸው ።
ቅንሽ ሥጋ ፡ እንደ መርፌ ትወጋ ።	ትወጋለች ።
ዝናብ ካልዘነበ ፤ ሁሉ ቤት እንግዳ ካልመጣ ሁሉ ሴት ።	ይባላል ፤ ትባላለች ።
ላም አለኝ ፤ በሰማይ ፤ ወተትዋንም አላይ ።	ግን ።
ተናካሽ ውሻ የኹብ መቋደሻ ።	ይሆናል ።
ጉፋያ ከመብላት ጮማ መሸከም ።	ን ፤ ይሻላል ።
ፍየል መንታ ትወልድ ፤ አንዱ ለወናፍ አንዱ ለመጽሐፍ ።	አለች፤ይሆናል። ነገር ግን ።

ክፍል ፲፩ ፡

የምሳሌዎች ሌላ ዓይነት አፈታት ፤

የምሳሌዎች ሌላ ዓይነት አፈታት የተባለው ምሳሌው እንዳለ ወይም ምንም ሳይስፋፋ ራሱ ሰም ይሆንና ሰሙንም ፡ በሚያህል አጭር አነጋገር ብቻ ወርቁን መፍታት ነው ። ይኸውም

ምሳሌው ፡ የምጣዱ ሳለ ፡ የቅንቅቡ ተንጣጣ ።
ፍቺው ፡ የተበደለ ዝም ብሎ ያልተበደለ አማረረ ።
ምሳሌው ፡ አይጥ ፡ በበላ ፤ ዳዋ ተመታ ።
ፍቺው ፡ ያጠፋ እያለ ፤ ያላጠፋ ተቀጣ ።
ምሳሌው ፡ ሰኞን አለመሆን ነው ።
ፍቺው ፡ አለ መቅደም ነው ።
ምሳሌው ፡ ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው ።
ፍቺው ፡ ለማይሠራ ሁሉም ነገር ቀላል ነው ።
ምሳሌው ፡ ኾበብ ከኼደ ውሻ ጮኸ ።
ፍቺው ፡ አንድ ነገር ከሆነ በኋላ መጸጸት አይጠቅምም ።
ምሳሌው ፡ ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ ።
ፍቺው ፡ ተስፋ አለኝ ግን ለችግሬ መፍትሔ አልሆነም ።

ምሳሌው ፡ የቆጡን አወርድ ብላ የብብትዋን ጣለች ።
ፍቺው ፡ የበለጠውን አገኛለሁ ፡ ብላ ፡ በእጅዋ የነበረውን አጣች ።
ምሳሌው ፡ ዕውር ሲቀናጣ ፤ ዘንጉን ወርውሮ ይፈልጋል ።
ፍቺው ፡ ነገር ያማረው ገንዘቡን አበድሮ ይሚገታል ።
ምሳሌው ፡ አትብዱ ያላት ወፍ በጥቅምት ዓይኗ ይጠፋል ።
ፍቺው ፡ ያልታደለ ሰው ሀብት ሲያገኝ ይሞታል ።
ምሳሌው ፡ የባሕር ዛፍ ከሥሩ ያለውን ችዶ ከሩቅ ያለውን ያጠላል ።
ፍቺው ፡ አላዋቂ ሰው ዘመዶቹ ጠማቸውን እያደሩ ፤ ገንዘቡን ለማንም ይለግሳል ።
ምሳሌው ፡ አፍንጫ ሲመታ ፤ ዓይን ያለቅሳል ።
ፍቺው ፡ አንዱን አንዱ ሲበድለው ፤ ወገኖቹ ይቀየማሉ ።
ምሳሌው ፡ ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ ።
ፍቺው ፡ ወረተኛ ከመውደዱ ወዲያው መጥላቱን ይቀጥላል ።
ምሳሌው ፡ ተናካሽ ውሻ የኾበብ መቋደሻ ።
ፍቺው ፡ ተንኳሽ ሰው የሞት ገፈታን ይቀምሳል ።
ምሳሌው ፡ ዓይን ካላዩበት ፤ ግንባር ነው ።

ፍቺው ፡ ዝምድና ካልተጠቃቀሙበት ባዕድነት ነው ።
ምሳሌው ፡ በሬ ካራጁ ጋራ ይኼዳል ።
ፍቺው ፡ ያላወቁ ከጠላቱ ጋራ ይኖራል ።
ምሳሌው ፡ ወዶ ገባ ልብሱ ዳባ ።
ፍቺው ፡ ተዋውሎ የፈረመ ግዴታውን መፈጸም አለበት ።
ምሳሌው ፡ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ።
ፍቺው ፡ ለውጥ የሌለው ሥራ ትርፉ ልፋት ብቻ ነው ።
ምሳሌው ፡ ቅወልዳለች ስላት ፤ ከነደሙ ከለከላት ።
ፍቺው ፡ ጭማሪን አገኛለሁ ስል ደመወዜንም ተከለከልሁ ።
ምሳሌው ፡ አነሰ ሲሉት ፤ ተቁረሰ ።
ፍቺው ፡ ለሌለው ፡ ያለችውን ይነሱታል ።
ምሳሌው ፡ ከዓጋም የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል።
ፍቺው ፡ ከክፉ ሰው የተጐራበተ ሲያዝን ይኖራል ።
ምሳሌው ፡ ጅራፍ እሷው ትገርፍ እሷው ትለፍፍ ።
ፍቺው ፡ ተንኰለኛ ሰው ራሱ በድሎ የተበደለ ያስመስላል ።
ምሳሌው ፡ ፈረስ ቢያነክስ ፤ አህያ ተኩስ ።
ፍቺው ፡ ኃይለኛ ቢበድል ፤ ደካማን ማጥቃት ።
ምሳሌው ፡ እርሾው ፡ ቢያምር ፡ ዳቦው ያምር ።

ፍቺው ፡ ባልና ሚስት ምስጥኖች ቢሆኑ ፤ ልጆቻቸው ቡሩካን ይሆናሉ ።
ምሳሌው ፡ በቦሃ ላይ ቆረቆር ።
ፍቺው ፡ በችግር ላይ ችግር ።
ምሳሌው ፡ ብርሌ ከነቃ ፡ አይሆንም ዕቃ ።
ፍቺው ፡ ታማኝ ከከዳ ፤ እንደ በፊቱ አይታመንም ።
ምሳሌው ፡ ተንጋልሎ ቢተፉ ፤ ተመልሶ ካፉ ።
ፍቺው ፡ ግብረ አበርን መንቀፍ ራስን ማዋረድ ነው ።
ምሳሌው ፡ ድር ቢያብር ፤ አንበሳን ያሥር ።
ፍቺው ፡ መተባበር ማንኛውንም ያሸንፋል ።
ምሳሌው ፡ በቅሎ ለኮዋን በጠሰች ፡ በራስዋ አሳጠረች ።
ፍቺው ፡ ጠቃሚውን ሰው የበደለ በራሱ ላይ ፈረደ ።
ምሳሌው ፡ አህያ የሌለው ፡ በቅሎ ይንቃል ።
ፍቺው ፡ ፊደልን ያልቆጠረ ሊቅን ይንቃል ።
ምሳሌው ፡ ሳይቃጠል በቅጠል ።
ፍቺው ፡ አንድን ጉጂ ነገር ሥር ሳይሰድ ፈጥኖ ማጥፋት ነው ።
ምሳሌው ፡ ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይጓዛል ።
ፍቺው ፡ ሰው ኗሪ ይመስል ለሁሉም ነገር ይንገበገባል።
ምሳሌው ፡ ዶሮ ፡ ጭራ ጭራ ፡ ታወጣለች ካራ ።
ፍቺው ፡ ሰው አዋቂ ሲሆን ፤ አጥፊውን ይሠራል ።



ከአለቃ ፡ ጽጌ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤